# የቅድስና ትውልድ

በኤፍሬም አለማየሁ ግንቦት 2011 ዓ.ም

ግንቦት 2011 ዓ.ም  በ ኤፍሬም አለማየሁ

ቴሌግራም @EphiSonJesus

ኢ-ሜይል - ephialex44@gmail.com

# የቅድስና ትውልድ

# ማውጫ


አላማ ..... 3
ዝግጅት ..... 4
ትምህርት ..... 5
ሳምንት አንድ ..... 5
ርዕስ፡ የመንግስት ለውጥ ..... 5
መንግስት ..... 6
የእግዚአብሔር መንግስት ..... 6
በብሉይ ኪዳን ..... 6
በአዲስ ኪዳን ..... 6
አንድ መንግስት የሚወከለው ባንዲራ አለው ..... 7
ታድያ ይህች የእግዚአብሔር መንግስት የት ናት? ..... 7
ሳምንት ሁለት ..... 8
ርዕስ፡ ሰውነት(ሰው መሆን) ..... 8
ሰውነት ለሀገር እና ለትዳር ..... 9
ሰው መሆን ለትዳር ..... 9
ከመፀሀፍ ቅዱስ የእውቀት ማዕዳችን እና ከግል ጥናቶች የተወሰደ ምክር ..... 10
፩. እጮኝነት ምንድር ነው? ..... 10
እጮኛ ለመያዝ ጊዜው መች ነው? ..... 10
በእጮኝነት ጊዜ መደረግ ያለባቸው ነገሮች፡- ..... 12
እጮኝነት ለስንት ጊዜ ይቆይ? ..... 13
፪. ትዳር ምንድር ነው? ..... 14
ትዳር መች ይጀመር? ..... 16
በትዳር ውስጥ የባል እና የሚስት ድርሻ ..... 16
ነ. የባል ድርሻ ..... 16
ባል ማወቅ ያለበት ሚስት ከርሱ የምትጠብቃቸው ሶስቱ ዋና ነገሮች ..... 18
ባል ስለ ሚስቱ ተፈጥሮ ማወቅ ያለበት ነገሮች፡- ..... 19
2. የሚስት ድርሻ ..... 20

# የቅድስና ትውልድ


ሰው መሆን ለሀገር ..... 24

ሳምንት ሶስት ..... 26

ርዕስ፡ ቅድስና ለእግዚአብሔር ..... 26

ከምን እንቀደሳለን? ..... 27

ለምን እንቀደሳለን? ..... 28

ልባርካቸሁ ..... 31

# አላማ

የዚህ ስልጠና ዋና አላማ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ጊቢ ውስጥ ያሉትን ክርስቲያን ተማሪዎችን በክርስቶስ ሕይወት(**ቅድስና**) ላይ ለማበርታት እና አላማ መር ሕይወት እንዲኖራቸው ለማጠንከር ነው፡፡ በዋነኝነት በህይወታቸው ከሚገጥሟቸው ሰይጣን ቅድስና ከሚያስጥልበት ከጋብቻ እይታ ግርታዎች፣ ፍራቻዎች እና በአምላካችን እግዚአብሔር ላይ ከሚነሳ ጥርጥር ነፃ ለማውጣት ነው። ከዚያም አልፎ በጊቢ ቆይታቸው ከልብ በመነጨ እውነተኛ ፍቅር እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉና እንደ ክርስቶስ በጎ ወታደር መከራን በትዕግስት እንዲቀበሉ ለማድረግ ነው፡፡

የዚህ ጽሑፍ መዘጋጀት ዋና አላማው ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች በዚህ ስልጠና ላልተገኙ ተማሪዎች እና ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ጊቢ ተማሪዎች ባሻገር ላሉ ለሀገሬ ኢትዮጵያ ወጣቶች የስልጠናውን ርዕስ እና ዋና ሀሳብ ለጥናት በሚመች መልኩ ማቅረብና በሰአት ምክንያት ያልተዳሰሱ ርዕሰ ጉዳዮችን በጥልቀት ለመዳሰስ ነው፡፡

የትኛውንም አይነት ጥያቄ ወይም አስተያየት በቴሌግራም @EphiSonJesus ላይ መፃፍ ወይም በ ephialex44@gmail.com ላይ ኢ-ሜይል ማድረግ ይቻላል።

# ዝግጅት

ሰው ካላወቀው ከተደበቀ ውንብድና እና ከኃጢአት ልምምድ በእግዚአብሔር ምህረት የዳንኩ አንድ የጌታዬ እና የአምላኬ የክርስቶስ ኢየሱስ ባርያ ኤፍሬም አለማየሁ ነኝ። በአሁኑ ወቅት የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ጊቢ የ2011 ዓ.ም ተመራቂ ተማሪ ነኝ። በዚህ የመጨረሻ የጊቢ ቆይታዬ መፀለይ እስኪከብደኝ ድረስ እግዚአብሔር አንድን ድምፅ በተደጋጋሚ አሰማኝ፤እርሱም “**ትውልድ ይቁደስልኝ፤ክብሬን እገልጣለሁ**” የሚል ነው። ከዚም በኋላ እንዴት ይህን መሬት ማውረድ እንደምችል እግዚአብሔር መንገዶችን አሳየኝ፤ አንዱም ይህን ስልጠና ለተከታታይ 3 ሳምንታት በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በመስጠት አህዱ ብሎ መጀመርን ነበር። ከዚያም ለህብረታችን መሪዎች በማሳወቅ ከየትኛውም የአገልግሎት ዘርፍ ጋር በማይጋጭበት ሁኔታ ለመስጠት ተስማማሁ። በዚህ መሰረት እሁድ ከቀኑ 5 ሰአት እስከ 7 ሰአት እንዲሰጥ ስምምነት ላይ ደረስን በዚህም መሰረት ተዘጋጀ።

# ኢየሱስ ብቻውን ይታይ!

# ትምህርት

## ሳምንት አንድ

### ርዕስ፡ የመንግስት ለውጥ

- **እግዚአብሔር ምናባዊ ብቻ ሳይሆን እውን የሆነ ሉአላዊ አምላክ ነው።። ዘፀ 3፥13-15**

“ሙሴም እግዚአብሔርን፦ እነሆ፥ እኔ ወደ እስራኤል ልጆች በመጣሁ ጊዜ፦ የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ላከኝ ባልሁም ጊዜ፦ ስሙስ ማን ነው? ባሉኝ ጊዜ፥ ምን እላቸዋለሁ? አለው።
እግዚአብሔርም ሙሴን፦ «ያለና የሚኖር» እኔ ነኝ አለው፤ እንዲህ ለእስራኤል ልጆች፦ «ያለና የሚኖር» ወደ እናንተ ላከኝ ትላለህ አለው።
እግዚአብሔርም ደግሞ ሙሴን አለው፦ ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ትላለህ፦ የአባቶቻችሁ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ እግዚአብሔር ወደ እናንተ ላከኝ፤ ይህ ለዘላለሙ ስሜ ነው፥ እስከ ልጅ ልጅ ድረስም መታሰቢያዬ ይህ ነው።”

- **እግዚአብሔር ለመማል ከርሱ በላይ ማንም ስለሌለ በራሱ ይምላል።። ዕብ 6፥13-14**

“እግዚአብሔርም ለአብርሃም ተስፋ በሰጠው ጊዜ፦ በእውነት እየባረክሁ እባርክሃለሁ እያበዛሁም አበዛሃለሁ ብሎ፥ ከእርሱ በሚበልጥ በማንም ሊምል ስላልቻለ፥ በራሱ ማለ፤”

# የቅድስና ትውልድ

- **ዘላለም ማለት አሜጋ ብቻ ሳይሆን አልፋ የሚባል መጀመሪያ የሌለው መጀመሪያ አለው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ አልፋን ኖሯል አሁንም አለ አሜጋንም ይኖራል፡፡ ዘለአለም የሚለው ቃል ሙሉ የሚሆነው እግዚአብሔር ጋር ብቻ ነው፡፡**
  **ራዕ 22፥13**

“አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።”

## መንግስት

- መንግስት ማለት ግንብ፣ካርታ ወይም ድንበር ሳይሆን ህዝቦች የሚገዙበት የአኗኗር ዘይቤ ነው፡፡
- በመንፈሳዊ አለም ላይ ሁለት መንግስታት አሉ፤ የእግዚአብሔር መንግስት እና የሰይጣን መንግስት ናቸው፡፡ስለሆነም በመዳናችን ያደረግነው የህይማኖት ለውጥ ሳይሆን የመንግስት ለውጥ ነው፡፡

## የእግዚአብሔር መንግስት

**በብሉይ ኪዳን**

በመወለድና የአብረሃም ዘር በመሆን ህግን በመጠበቅና በመገረዝ የእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ **በከፊል** መግባት ይቻላል፡፡

**በአዲስ ኪዳን**

በተከፈተውና በተመረቀልን በአዲሱ በር በኢየሱስ በማመን **ብቻ** ወደ መንግስቱ **በሙላት** መግባት ይቻላል፡፡

# የቅድስና ትውልድ

ዕብ 10፥19-20

“እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፥…”

## አንድ መንግስት የሚወክለው ባንዲራ አለው

- የእግዚአብሔር መንግስት **የፅድቅ** ባንዲራ
- የሰይጣን መንግስት **የኃጢአት** ባንዲራ

በአንዱ መንግስት ውስጥ ሆኖ የሌላውን ባንዲራ ማውለብለብ ክልክል ነው፡፡ ስለሆነም በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ሆኖ የኃጢአት ባንዲራ ማውለብለብ **ክልክል** ነው፡፡

## ታድያ ይህች የእግዚአብሔር መንግስት የት ናት?

በመሀከላችን ናት!

ሉቃ 17፥20-21

“ፈሪሳውያንም፦ የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች ብለው ቢጠይቁት፥ መልሶ፦ የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም፤ ደግሞም፦ እንኋት በዚህ ወይም፦ እንኋት በዚያ አይሉአትም። እነሆ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት **በመካከላችሁ ናትና** አላቸው።”

# የቅድስና ትውልድ

## ሳምንት ሁለት

**ርዕስ፡ ሰውነት(ሰው መሆን)**

**1ነገ 2፥3**

“በርታ ሰውም ሁን፤ የምታደርገውንና የምትሄድበትን ሁሉ ታከናውን ዘንድ፥ በሙሴ ሕግ እንደ ተጻፈ ሥርዓቱንና ትእዛዛቱን ፍርዱንና ምስክሩንም ትጠብቅ ዘንድ፥ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ፥ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ።”

- **ሰውነት የሚጀምረው በትህትና እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ነው።**
- **እግዚአብሔር ሰው ለሆነለት ሰው ጥብቅና ይቆማል።**

**ዘኁ 12፥8**

“እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ፥ በምሳሌ አይደለም፤ የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል፤ በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለ ምን አልፈራችሁም? አለ።”

**ዘፍ 6፥18**

“ቃል ኪዳኔንም ከአንተ ጋር አቆማለሁ፤ ወደ መርከብም አንተ ልጆችህንና ሚስትህን የልጆችህንም ሚስቶች ይዘህ ትገባለህ።”

# የቅድስና ትውልድ

## ሰውነት ለሀገር እና ለትዳር

**ሰው የሆነ ሰው ቅድስና አርማው ነው ፤ እግዚአብሔር ዋናው ነው።**

## ሰው መሆን ለትዳር

**ሰው የሆነ ሰው፡-**

- **ትዳር በአማኝ እና በአማኝ መሀከል ብቻ በተቃራኒ ፆታ የሚደረግ የህይወት ዘመን ቃልኪዳን እንደሆነ ያምናል።**
- **ለንፁሕና ለቅዱስ ጋብቻ ክብር አለው።**
  - **ዕብ 13፥4**
    - “መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።”
- **ለጋብቻ እውነተኛ ምሳሌው የክርስቶስ እና የቤ/ክ ህብረት ነው።**
  - **ኤፌ 5፥21-26**

“ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ።
ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤
ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና።
ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ።
ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤”

# የቅድስና ትውልድ

## ከመፀሀፍ ቅዱስ የእውቀት ማዕዳችን እና ከግል ጥናቶች የተወሰደ ምክር

- ከየትኛውም ተቃራኒ ፆታ ጋር ባለን ግንኙነት ህብረታችን ስም ሊኖረው ይገባል። ለምሳሌ ወንድሜ ፣ እህቴ ፣ አባቴ ፣ እናቴ ፣ ክላስ ሜት ፣ እጮኛ ፣ ባል ፣ ሚስት የመሳሰሉትን መባል አለበት። ነገር ግን ምንሽ ነው?/ምንህ ናት ለሚለው ጥያቄ ምኔም አይደለም ወይም ምኔም አይደለችም የሚሉ መልሶች ራስን ያልተገባ ውዝግብ ውስጥ ይከታሉ። ለተጓዳኝና ላልተፈለጉ ህይወቶች ምክንያት ይሆናሉ። በዚሁ ሳልጠቅስ ማላልፈው ነገር Boy Friend እና Girl Friend የሚባሉ ግንኙነቶች በአሁኑ ሰአት በዝተዋል። ነገር ግን እንደ መንፈሳዊ እና እንደ ባለ አዕምሮ ስናስበው ወንዱ Girl Friend ሳይሆን Woman Friend ሴቷ ደግሞ Boy Friend ሳይሆን Man Friend ያስፈልጋቸዋል። ምክንያቱም ቃሉ እንደሚያመለክተው Boy እና Girl ሮጠው ያልጨረሱ ህፃናት እንደሆኑና ቁም ነገር ላለው ህይወት እንደማይመጥኑ ነው። ነገር ግን ወንዱ Man እና ሴቷ Woman ሲሆኑ ትክክለኛ አላማ እና እውነተኛ ህይወት ለመምራት ያላቸውን የአዕምሮ እድገት ያሳያል። አልያ ግን እርሱም ህፃን እንደሆነ እና እርሷም ህፃን እንደሆነች ያሳያል።

## ፩. እጮኝነት ምንድር ነው?

- እጮኝነት ማለት በአማኝና አማኝ ብቻ በተቃራኒ ፆታ መሀከል በቅድስና የሚደረግ ግንኙነት ሲሆን ቆይታው እስከ ጋብቻዋ እለት ድረስ ብቻ ነው።
- እግዚአብሄር በእጮኝነት ውስጥ ወንድ እና ሴት እንዲተዋወቁም ሆነ ምንም አይነት ያልተገባ ንክኪ እንዲያረጉ ፈቃዱን አልሰጠም።

## እጮኛ ለመያዝ ጊዜው መች ነው?

- እጮኛ ለመያዝ የእድሜ እና ይሄ ነው የሚባል እርግጥ የሆነ ሰአት የለውም። ነገር ግን ብስለትን ይሻል። መሟላትም ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አሉ።

# የቅድስና ትውልድ

- **መጀመርያ ሁሉም ነገር ከራስ እንደሚጀምር መታወቅ አለበት። ጉድለት ለመሙላት እጮኝነትንና ትዳርን ማሰብ ተገቢ አይደለም። ወንዱ የራሱ ከሚላት ሴት የሚፈልገውን ቅንነት ፣ ፍቅር ፣ የዋህነት ፣ እግዚአብሔርን መፍራት እና መታዘዝን መጀመርያ ራሱ ማድረግ አለበት ፤ ሴቷም ከወንዱ የምትፈልገውን ቅንነት ፣ ፍቅር ፣ የዋህነት ፣ እግዚአብሔርን መፍራት እና መታዘዝን ራሷ ማድረግ አለባት። የማትወደውን ወይም የማትወጅውን የራስ ባህሪ በእጮኛዬ ምክንያት ተወዋለው ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው። ይልቁንም ከእጮኝነት በፊት በራስ ላይ ያለን አላስፈላጊ ባህሪ ማስወገድ እና ብቁ ሆኖ መገኘት ተገቢ ነው።**
- **ራስህ/ሽ ሰው ስትሆን/ኚ**
  - **ወንድ፦**
    - **ባለ ራዕይ ሊሆን ይገባል።**
    - **ሴትን ከማግኘቱ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። ዘፍ 2፥16**
      - “እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤”
  - **ሴት፦**
    - **ልቧ የተሰበረ ሊሆን ይገባል።**
    - **ወንድን ከማግኘቷ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ሊኖራት ይገባል።**
      - **ብዙዎች እንደሚያስቡት ሔዋን በመጀመርያ አዳምን ሳይሆን ያየችው አምላኳን እግዚአብሔርን ነው። ምክንያቱም በ ዘፍ 2፥22 ላይ** “እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት፤ ወደ አዳምም አመጣት።” **የሚለው ቃል ከአዳም በፊት ሌላ ቦታ እንደነበረችና መጀመርያ እግዚአብሔርን እንዳየች ያስገነዝበናል።**

- ልባም እና እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት መሆን አለባት። ምሳ 31÷10-12 ፣ ምሳ 31÷28-30

○ በትክክል የእግዚአብሔር ፈቃድ ያለበት/ባትን ሰው የሆነን ሰው ከራሱ ከእግዚአብሔር ሲገኝ መሆን አለበት።

○ ሰአቱን በትክክል ከእግዚአብሔር በመጠየቅ በሰአቱ መጀመር።

- ምክንያቱም አንድ ህፃን በልጅነቱ ነብይ እንደሚሆን እግዚአብሔር ተናገረ ማለት ልጁ የዚያውኑ ሰአት እንደማይሆንና በብዙ ብስለትና በእግዚአብሔር ሰአት እንደሚፈፀም ሁሉ እግዚአብሔር የትዳር አጋርን አሳወቀን ማለት እጮኝነት ለመጀመር ፈቃድ ሰጠ ማለት አለመሆኑን ተረድቶ ትክክለኛ ሰአቱን ከራሱ ከተናገረው ከእግዚአብሔር መስማትና ማወቅ አለብን።

## በእጮኝነት ጊዜ መደረግ ያለባቸው ነገሮች፦

- ሸሸ ከእጮኛም እንደሆነ በመረዳት እስከ እለተ ጋብቻ ድረስ በቅድስና እና እግዚአብሔርን በመፍራት መመላለስ ይገባል።
- ድንግልና የሚታጣው ሳይንሱ እነደሚለው በመተኛት ውስጥ በሚሆነው የደም ስሮች መበጠስ ሳይሆን ገና በመመኘትና ባልተቀደሰ ንክኪ እንደሆነ በመገንዘብ የትኛውንም ያልተቀደሰ ምኞትና ንክኪ ማስወገድ ይገባል። ይልቁንም በርቀት በመሆን በመፀለይ እና ለመገናኘት ሲታሰብም ተገቢውን ቦታ እና ሰአት በመምረጥ መገናኘት ተገቢ ነው።
- እጮኝነቱን ለመጠበቅና በጸሎት ለመደገፍ ሲባል ቤ/ክ ፣ ቤተሰብ እና አቅራብያ ላይ ያሉ ሻል ያለ እውቀት ያላቸው ሰዎች መስማት አለባቸው።
- ባሌ እና ሚስቴ የሚሉ ቃሎችን ማስወገድ ያስፈለጋል። ምክንያቱም እኚህ ቃሎች ለመተኛት ፈቃድን ይሰጣሉ። ከመባል በፊት መሆን ስለሚቀድም ባሌ ወይም ሚስቴ የሚሉ ቃሎችን ከመሆን በፊት መጠቀም ተገቢ አይደለም። ባል ወይም ሚስት  የሚኮነው ደግሞ ከጋብቻ እውነተኛ ቃል ኪዳን በኋላ ነው።

# የቅድስና ትውልድ

- በእጮኝነት ወራት ብዙ እጮኛችንን ከማግኘትና ለብዙህ ሰአት ከማውራት ይልቅ ወደ እጮኛችን እናት፣አሳዳጊ ወይም የልብ ጓደኛ በመሄድ እውነተኛ ድካሙንና ብርታቱን በመጠየቅና በማስተዋል ለቀጣይ ኑሮ መዘጋጀት ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን ግን ለእጮኛችን ባለን የጥርጣሬ ልብ ሳይሆን በንፁህ ህሊና መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው።
- ወንዱ ሴት እጮኛውን ማክበርና ንጽህናዋን መጠበቅ አለበት። ለመተኛትና ለየትኛውም ንክኪ ጥያቄ ብታቀርብለት እንኳ እርሱ መሸሽ አለበት። ምክንያቱም በሰርጓ ቀን ያደረገችው ልበስ ነጭ እንደሆነ ውስጧም ንጹሕ እንዲሆን የሚከፍላት ውለታው ነው። እሷን መውደዱንና ማክበሩን እሷን ባለመንካት እና ንጽሕናዋን በመጠበቅ ሊያሳያት ይገባል። እርሷም ለእርሱ እንደዚሁ መሸሽ ይኖርባታል።

## <u>እጮኝነት ለስንት ጊዜ ይቆይ?</u>

- እጮኝነት ከ 6 ወር እስከ 2 አመት ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ ትዳር ቢያድግ ይመረጣል። ምክንያቱም ከ 6 ወር ካነሰ ለትዳር በቂ የሆነ ዝግጅት እንዳይኖር ምክንያት ሊሆን ይችላል፤ እንዲሁም ደግሞ ከ 2 አመት ከበለጠ ለተለያዩ ፈተናዎችና የእምነት መጓደሎች ምክንያት ሊሆን ይችላል።

# የእጮኝነት ጊዜአችሁ በቅድስና እና እግዚአብሔርን በመፍራት በፀሎት የተባረከ ይሁን!!

## ፪. ትዳር ምንድር ነው?

- **ከላይ እንደተጠቀሰው ትዳር ማለት በአማኝ እና በአማኝ ብቻ በተቃራኒ ፆታ መሀከል የሚደረግ የህይወት ዘመን ቃልኪዳን ሲሆን ለመቀበል ሳይሆን ለመስጠት ታስቦ የሚገባበት ተቋም ነው። ይህን ኪዳን ማንም ምንም አይነት ምክንያት ቢኖርም ማፍረስ አይቻልም፤**
    - **ማቴ 19፥3-6**

“ፈሪሳውያንም ወደ እርሱ ቀረቡና ሲፈትኑት፦ ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? አሉት።
እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አለ፦ ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፥ አለም፦ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?
ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው።”

- **በእርግጥ ስለ ልባቸው መደንደን በዝሙት ምክንያት መፍታት እንደሚችሉ ነግሮአቸዋል፤ ይህን ግን ያላቸው ስለ ልባቸው መደንደን ሲል ነው፤ የእግዚአብሄር ልብ ግን መፋታትን ይጠላል።**

    - **ማቴ 19፥8-9**

“እርሱም፦ ሙሴስ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፤ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም።
እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል አላቸው።”

# የቅድስና ትውልድ

- **ትዳር በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረ ነው፤ ምክንያቱም በመጀመርያ የትዳር ጠንሳሽ ራሱ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።**
    - **ዘፍ 2፥24**

“ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።”

- **እግዚአብሄር በትዳር ውስጥ ባል እና ሚስት እንዲተጉ ሙሉ ፈቃድ ይሰጣል፤ መኝታውም ንፁሕ እንዲሆን ይፈልጋል። እንዲህ ባለ ንፁሕ ግንኙነት ልቡ ደስ ይለዋል ደግሞም ያከብረዋል።**
    - **ዕብ 13፥4**
        - “መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤”

- **ትዳር የክርስቶስ እና የቤ/ክ ምሳሌ ስለሆነ ከመኝታ ያለፈ አላማ አለው፤ ትውልድ የሚቀጥልበት እውነተኛ ህይወትንና እውነተኛ አምልኮ ያለበት በመንፈስ ቅዱስ አንድነቱ የሚጠበቅ ከእግዚአብሔር የሆነ ተቋም ነው።**
    - **ኤፌ 5፥21-26**

- **ትዳር በሙሉ እምነት ላይ መመስረት ይኖርበታል። ባል ሚስቱን በሙሉ ልቡ ማመን ይኖርበታል ሚስትም እንደዛው። በመሀከላቸው አለመተማመን ካለ ለትዳሩ መሰረት መሰንጠቅና መፍረስ ቀዳሚ ምክንያት ነው።**

# የቅድስና ትውልድ

## ትዳር መች ይጀመር?

- ሁለት እጮኛሞች እጮኝነታቸው ወደ ትዳር እንዲያድግ ካሰቡ ወንዱ "በዚህ ሰአት እውነተኛ ባል እና በመውለድ ትክክለኛ አባት ለመሆን ብቁ ነኝ?" የሚለውን ጥያቄ ለራሱ ሲመልስ እና ሴቷ ደግሞ "በዚህ ሰአት እውነተኛ ሚስት እና በመውለድ ትክክለኛ እናት ለመሆን ብቁ ነኝ?" የሚለውን ጥያቄ ለራሷ ስትመልስ ለትዳር ብቁ ናቸው ማለት ነው።
- ከቤተሰብ ወይም ከአሳዳጊ ትከሻ ላይ የሚወርዱበትና ተነጥለው ለመኖር የሚሆናቸው ትንሽ ነገር ሊኖራቸው ይገባል።

## በትዳር ውስጥ የባል እና የሚስት ድርሻ

### ነ. የባል ድርሻ

- ባል ባለ ራዕይ መሆን አለበት። ባለ ራዕይ መሆን ማለት በእግዚአብሔር ጠንሳሽነት በራስ ጀማሪነት በሌሎች እርዳታ ለሚደረግ ጉዞ እስከ ሞት ድረስ የምንታገልለት ከእግዚአበሔር የተቀበልነው ዓላማ ነው። ስለዚህ ባል ይህን አይነት ራዕይ ከትዳር ዘመኑ በፊት ከእግዚአብሔር ሊቀበል ይገባዋል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሚስትን ሲሰጠው የሚመቸው ረዳት እንድትሆን አስቦ ነውና ራዕይ ሊኖረው የተገባ ነው። ነገር ግን ራዕይ ከሌለው በምን ልትረዳው ትችላለች? ይህ ጥያቄ ማስተዋል ተገቢ ነው። ስለዚህ አንድ ወንድ ባል ከመሆኑ በፊት ራዕይ ሊኖረው ይገባል። አዳም ሔዋንን ከማግኘቱ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ሙሉ ግንኙነት ነበረው፤ ምድርን እንዲገዛ ከእግዚአብሔር ራዕይን ተቀብሎአል፤ በስራ ላይም ነበረ ለእንስሳት ሁሉ ስምን አውጥቷል፤ ለዚህ ራዕይ ደግሞ እግዚአብሔር የሚመቸውን ረዳት ሰጠው። ስለዚህ አንድ ወንድ ከሚስት በፊት እግዚአብሔርና ራዕይ እንደሚቀድም ማወቅ አለበት።

# የቅድስና ትውልድ

- ዘፍ 2፥18
  - “እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።”

- **ባል የሚስቱ ራስ መሆኑ ገብቶት ቤቱን(አካሉን) እንዴት ማስተዳደር እንዳለበት ከእግዚአብሔር ጥበብና ማስተዋልን መጠየቅና መቀበል አለበት፤ እንዲሁም ክርስቶስ ቤ/ክ እንደወደደ እንዲሁ ሊወዳት ይገባል ይህም መፀሀፍ ቅዱሳዊ ነው።**

- **ባል ሚስቱ ጥያቄዎችን ስትጠይቀው ጭቅጭቅ እንደሆነ ከማሰብ ይልቅ ሙሉ እና እውነተኛ መልስ መመለስ አለበት፤ ምክንያቱም የርሱን ራዕይ በጥልቀት ልትረዳ ምትችለውና ባሰበው ነገር ላይ እውነተኛ ረዳት ልትሆነው የምትችለው ስትጠይቀውና ስለርሱ የልብ ሀሳብ በጥልቀት ስታውቅ እንደሆነ መረዳት አለበት።**

- **ባል ከሚስቱ የሚደብቀው ምንም አይነት ሚስጥር ሊኖረው አይገባም። ሁሉን ሊነግራትና ሊያማክራት ይገባል። የባንክ ሂሳቡን፣የስልኩን ሁሉ Password እና ሌሎችንም ሊያጋራት ይገባል። ከዚህም አልፎ ሚስቱ ማታውቃትን ሴት በተደጋጋሚ ማግኘት የለበትም፤ ማግኘት ካለበትም ለሚስቱ አስተዋውቋት ከዛም በበቂ ምክንያት በትክክለኛ ቦታ እና ሰአት ማግኘት አለበት።**

- **ባል ከሚስቱ ውጪ ያለችን ሴት በምንም አግባብ በሚስቱ ፊት ከርሷ አብልጦ ማጉላትና ማሞካሸት የለበትም። ይህን የሚያደርግ ከሆነ ከሚስቱ ልብ ጫና፣ ያለመፈለግና የትንሽነት ስሜትን በስተመጨረሻም ደግሞ ጥርጣሬንና አለመታመንን ያጭዳል። ስለዚህ አስተዋይ ባል ሚስቱ ዘውዱ ናት፤ ስለሌላ ሴት ከማሰብና ሌላዋን ከማጉላት ይልቅ ያለውን ሰአት ሚስቱን እንዴት በይበልጥ እንደሚወድና እንደሚያስደስታት በማሰብ አምላክ ያዘዘውን የክርስቶስን ፍቅር በመፈፀም ራስነቱን ያሳያል። ለዚህ አስተዋይ ባል ደግሞ ከንጹህ ልብ የሆነ እውነኛ መገዛት ከሚስቱ ዘንድ ይጠብቀዋል።**

# የቅድስና ትውልድ

- ክርስቶስ ቤ/ክንን እንደወደደ ባል ሚስቱን መውደድ አለበት፤ ክርስቶስ እኛ ቤቱ የሆነውን የማረንን ያህል ሚስቱን ሊምራት ይገባል። ክርስቶስ እስከሞት እንደወደደን ባልም እንዲሁ ሚስቱን ሊወዳት ይገባል።

- ሚስት በአፏ አውጥታ ባትናገርም በስነ-አፈጣጠሯ በውስጧ ከባሏ ሶስት ነገሮችን ትፈልጋለች ትሻለች፦

<u>ባል ማወቅ ያለበት ሚስት ከርሱ የምትጠብቃቸው ሶስቱ ዋና ነገሮች</u>፦

- Security, Communication and Affection ናቸው።

  - <u>Security</u>፦
    - ሚስት ከባልዋ ጥበቃን ትሻለች፤ ይህ ማለት በምታረጋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ የት ገባሽ የት ወጣሽ መባልን ሳይሆን በሀሳብ፣በጉልበት እና በአቋም ባሏ ከለላ አንዲሆንላት አልፎም እንዲያበረታት ትሻለች።

  - <u>Communication</u>፦
    - ሚስት ባልዋ በነገሮች ሁሉ ሳታወራ እንዲረዳት እና ሙሉ በሙሉ እምነቱን እንዲያሳድርባት ትሻለች፤ ጥርጣሬን በመሀከላቸው አትሻም።

  - <u>Affection</u>፦
    - Affection ከመተኛት ጋር ትልቅ ልዩነት አለው፤ Affection ማለት የፍቅርን ቃል መንገርና ሚስት የምትወደውን የስጦታ አይነት አጥንቶ መስጠት ማቀፍና የመሳሰሉትን የሚያካት ነው። ስለዚህ ባሎች ሊረዱት የሚገባው ነገር ቢኖር ሚስት ከባሏ ጋር ከመተኛት ይልቅ ከባሏ Affection በይበልጥ ትሻለች።

# የቅድስና ትውልድ

## ባል ስለ ሚስቱ ተፈጥሮ ማወቅ ያለበት ነገሮች፡-

- ሚስቱ የቤቱ ነብይት እንደሆነች ማወቅ አለበት። ነብይ ከእግዚአብሔር የሰማውን እንደሚናገር እና ህዝብን እንደሚያጽናና የደከመውን ኃያል እንደሚያበረታ ልክ እንደዛ ሚስት ከራሱ ከባሏ በብርታቱ ጊዜ የሰማችውን በደከመ ጊዜ ደግማ ትነግረዋለች፤ ስለዚህ በዚያን ሰአት ባል ሚስቱ እየጨቀጨቀችው እንደሆነ ከማሰብ ይልቅ ደግማ ስለነገረችውና ስላበረታችው ሊያመሰግናትና በዚህም ምክንያት አብልጦ ሊወዳት ይገባል።

- ሚስቱ 100% ከርሱ ተቀባይ ሆና እንደተፈጠረች ማመን አለበት።

- ሚስቱ Incubator እንደሆነች ማወቅ አለበት። Incubator በራሱ ምንም አያደርግም፤ ይልቁንም እኛ ያስገባለትን ነገር አሳድጎ መልሶ ይሰጠናል፤ ልክ እንዲሁ ሚስት ከባልዋ የተቀበለችውን ያንኑ ነገር አብዝታ መልሳ ትሰጠዋለች። ፊደል ቢሰጣት ቃል፣ ቃል ቢሰጣት ሐረግ ፣ሐረግ ቢሰጣት አረፍተ-ነገር፣ አረፍተ-ነገር ቢሰጣት ገጽ ፣ ገጽ ቢሰጣት ደግሞ መጸሀፍ አድርጋ ትሰጠዋለች፤ አንድ የወንድ ዘር ተቀብላ ልጅ አድረጋ ትሰጠዋለች፤ አንድ ስድብ ቢሰጣት ብዙ ስድብ እንዲሁም አንድ ፍቅር ቢሰጣት ብዙ ፍቅር ትሰጠዋለች። በእርግጥ ክርስትያን ከሆነች ላታወራ ወይም ላትሳደብ ትችላለች፤ ነገር ግን አእምሮዋ ይህን ማሰቡ ግድ ነው። ስለዚህ ባል ከሚስቱ መጥፎን ነገር እያገኘ ከሆነ እርሷን ከመውቀስ ይልቅ ለሷ የሚሰጣትን ነገር ማስተካከል አለበት።

## 2. የሚስት ድርሻ

- ሚስት ምንም አይነት የራሷ የሆነ የምታስበው ራዕይ ቢኖራትም በደመወዝ ከርሱ ብትበልጥም ለባሏ ራዕይ ግድ መገዛት አለባት፤ እውነተኛ ረዳቱ ልትሆን ይገባታል፤ ምክንያቱም ለባልዋ ረዳት ሆና ተፈጥራለችና።

  - ሚስት ከባልዋ የምትደብቀው ምንም አይነት ሚስጥር ሊኖራት አይገባም። ሁሉን ልትነግረውና ልታማክረው ይገባል። የባንክ ሂሳቧን፣የስልኳን ሁሉ Password እና ሌሎችንም ልታጋራው ይገባል። ከዚህም አልፎ ባልዋ ማያውቀውን ወንድ በተደጋጋሚ ማግኘት የለባትም፤ ማግኘት ካለባትም ለባልዋ አስተዋውቃ ከዛም በበቂ ምክንያት በትክክለኛ ቦታ እና ሰአት ማግኘት አለባት። ይህን ማታደርግ ከሆነና ምን ይመጣል የሚል የግለኝነት ስሜት ካላት ሳታውቀው ባልዋን ከርሷ ጎን ቀስበቀስ ታጣዋለች። በመሉ ልቧ ባልዋን መውደዷን ለማሳየት ከርሱ የምትደብቀው ምንም ሚስጢር ሳይኖራት ሁሉን ለርሱ ብቻ ግልጥ ልታደርግለት ይገባል። በዚህም የባልዋን ልብ መማረክና መግዛት ትችላለች።

- ሚስት ባልዋ የሷ ራስ እንደሆነ ማመን አለባት፤ ምክንያቱም ቤተ-ክርስትያን የክርስቶስ ራስ መሆን እንደማትችለው ሁሉ ሚስትም የባልዋ ራስ መሆን አትችልም። ራስ ለመሆን ብታስብ በአንድ አካል ላይ ሁለት ራስ ሲኖር ሌላ ፍጥረት እንደሚባለው ልክ እንደዛ ጋብቻው ሌላ መልክ ይይዛል። ስለዚህ ባሏን እንደ ራስ ከማዘዝና ከመምራት ይልቅ በልበ ቅንነት ከባሏ የሚመጡትን ሃሳቦች በመቀበል ልታስተናግድና ልትገዛ ይገባታል። ምክንያቱም ሚስት ከባልዋ አትበልጥምና።
    - ነጢሞ 2፣11-13

“ሴት በነገር ሁሉ እየተገዛች በዝግታ ትማር፤
ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን አልፈቅድም።
አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአልና፥ በኋላም ሔዋን ተፈጠረች።”

# የቅድስና ትውልድ

- ሚስት በእርግጥ በተፈጥሮ ሴት እንደመሆኗ መጠን ብዙ ፍላጎቶች እንዳላት ተረድታ በእነዚህ ፍላጎቶቿ ባሏን ከአቅሙ በላይ ማስጨነቅ እንደሌለባት በማወቅ ለፍላጎቶቿ ገደብ ማበጀት ይኖርባታል። ነገር ግን እንደ አስተዋይ ሴት ባሏን እያበረታችውና በትክክል በራዕዩ እየደገፈችው ፍላጎቶቿ ላይ እንዲደርስ እና እንዲያሟላላት በማድረግ ልባም ልትሆን ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም ልባም መሆኗ ለባሏ ዘውድ ያደርጋታል።
    - ምሳ 12÷4
        - “ልባም ሴት ለባልዋ ዘውድ ናት፤ አሳፋሪ ሴት ግን በአጥንቱ ውስጥ እንደ ቅንቅን ናት።”

- ሚስት ባልዋን ጥበብ በሞላበትና በጥልቀት አሉታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለባት። ምክንያቱም ስለ ባልዋ የልብ ሀሳብ ከማንም በላይ በጥልቀት በማወቅ ራዕዩን በሙሉ ልብ መደገፍ የሷ ብቻ ድርሻ ነው። ነገር ግን ባልዋን በሙሉ ልብ አውቀዋለው በሚል ስሜት ጥያቄ ባቆመች መጠን ልክ ባሏን ታጣዋለች፤ ምክንያቱም የት ጋር እንደምትረዳው በትክክል የልቡን ሃሳብ ስለማታውቅ ከርሷ ውጪ ሌላ ረዳት ከውጭ መፈለግ ይጀምራል። ስለዚህ መጠየቋ ማነሷ ሳይሆን ባሏ ያለበትን ሁኔታ በማወቅ ሳይረፍድ በሰዐቱ ትክክለኛ እርዳታ እንድትሰጥ ያስችላታል። አልያ ግን ይህን ካላረገች ባይነግራትም በባሏ ዘንድ ዋጋዋ ትንሽ ይሆናል።

- ሚስት በልቧ የምታስበውን ሁሉ ምንም ሳታስቀር በነጻነት ለባሏ መናገር አለባት፤ ያውቀዋል ብላ የምታስበውንም የማያውቀውንም ጭምር። በባልዋ ዘንድ ጠንካራ ሴት የምትባለው ሀሳቧን በልቧ ደብቃ የምትይዝና ጠንካራ እንደሆነች የምታሰበው ሳትሆን በሙሉ የልቧን አውጥታ ለርሱ የምትነግረውና ምክሩንና እርዳታውን የምትጠይቀው ናት። ምክንያቱም ክርስቶስ የእርሱ ቤ/ክ ስለሆነው ስለ እኛ ሁሉን ያውቃል፤ ነገር ግን ቢያውቅም በጸሎታችን ስላለንበት ነገር እንድንነግረው ይሻል። ልክ እንዲሁ ባልም ከሚስቱ ይህን ይሻል፤ ቢያውቅም ሚስቱ ስላለችበት እና ስለምታስበው ነገር መስማትን ይፈልጋል። እነዲሁም እኛ በክርስቶስ ፊት በምንሆንበት ጊዜ ጥንካሬአችንን እና ጽድቃችንን

# የቅድስና ትውልድ

እንደማናወራ በፊቱ መሰዋዕቱ ግልጥ እንደሆነና እረዳታውን እንደምንጠይቀው ልክ እንደዚሁ ሚስት ለባልዋ ሁሉን መናገርና ምክርን እርዳታውን መጠየቅ ይጠበቅባታል። አልያ ግን ባሏ በርሷ ዘንድ ቦታ እንደሌለው ያስባል። ስለዚህ ባሏን ምትወደውና ምታፈቅረው ከሆነ በርሷ ዘንድ ቦታ እንዳለው ከመናገረ ባለፈ በተግባር በዚህ መንገድ ያለውን ቦታ እና ለርሱ ያላትን አክብሮቷን ልታሳየው ይገባል።

- ሚስት ባሏ ለርሷ 100% ሰጪ እንደሆነ እና እርሷ ደግሞ 100% ከርሱ ተቀባይ እንደሆነች ማመን አለባት። ይህ ሲባል ግን ምንም አትስጠው ማለት ሳይሆን ባልዋ ለሷ ሙሉ በሙሉ ሰጪ እንደሆነ ትመን ማለት ነው።

- ሚስት ከባልዋ ውጪ ያለን ወንድ በምንም አግባብ ከባልዋ አብልጣ ማጉላትና ማሞካሸት የለባትም። ይህን ምታደርግ ከሆነ ከባልዋ ልብ ላይ ጫና፣ ያለመፈለግና የትንሽነት ስሜትን በስተመጨረሻም ደግሞ ጥርጣሬንና አለመታመንን ታጭዳለች። ስለዚህ ለብልህ ሴት ባልዋ ለርሷ ንጉሷ ነው፤ ስለሌላ ወንድ ከማሰብና ሌላውን ከማጉላት ይልቅ ያላትን ሰአት የባልዋን እንከን እንዴት እንደምትሸፍን በማሰብና ባልዋን ወደ ራዕዩ እንዲደርስ በማበርታት እውነተኛ ረዳትነቷን ታሰላያለች። ለዚህች ሴት ምስጋና ከባልዋ ዘንድ ይጠብቃታል።

- ሚስት በቤቷ ላይ Manager እንደሆነችና በትክክል ይህን ስራዋን መወጣቷ በባልዋ ዘንድ ትልቅ ቦታ እንዳለው ማወቅ አለባት፤ ቤቷን በጥበብ መምራቷ፣ ልጆችን በጥበብ ማሳደጓ በባሏ ዘንድ ልባም ሴት ያስብላታል፤ ባልዋም ስለ እርሷ በአደባባይ ይናገራል ፣ይታመንባታል ፣ ያሞግሳታል ዘውዴ ይላታል። አልያ ግን በሰዎች መሃል ያፍርባታል ስለ እርሷ ሊናግር አይደፍርም።
    - ምሳ 31፥10-31

“ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቁ እጅግ ይበልጣል። የባልዋ ልብ ይታመንባታል፥ ምርኮም አይጐድልበትም።

# የቅድስና ትውልድ

ዕድሜዋን ሙሉ መልካም ታደርግለታለች፥ ክፉም አታደርግም።
የበግ ጠጕርና የተልባ እግር ትፈልጋለች፥ በእጆችዋም ደስ ብሎአት ትሠራለች።
እርስዋ እንደ ነጋዴ መርከብ ናት፤ ከሩቅ አገር ምግብዋን ትሰበስባለች።
ገና ሌሊት ሳለ ትነሣለች ለቤትዋም ሰዎች ምግባቸውን፥ ለገረዶችዋም ተግባራቸውን ትሰጣለች።
እርሻንም ተመልክታ ትገዛለች፤ ከእጅዋም ፍሬ ወይን ትተክላለች።
ወገብዋን በኃይል ትታጠቃለች፥ ክንድዋንም ታበረታለች።
ንግድዋ መልካም እንደ ሆነ ትመለከታለች፤ መብራትዋ በሌሊት አይጠፋም።
እጅዋን ወደ አመልማሎ ትዘረጋለች፥ ጣቶችዋም እንዝርትን ይይዛሉ።
እጅዋን ወደ ድሀ ትዘረጋለች፥ ወደ ችግረኛም እጅዋን ትሰድዳለች።
ለቤትዋ ሰዎች ከበረዶ ብርድ የተነሣ አትፈራም፥ የቤትዋ ሰዎች ሁሉ እጥፍ ድርብ የለበሱ ናቸውና።
ለራስዋም ግብረ መርፌ ስጋጃ ትሠራለች፤ ጥሩ በፍታና ቀይ ግምጃ ትለብሳለች።
ባልዋ በአገር ሽማግሌዎች መካከል በሸንጎ በተቀመጠ ጊዜ በበር የታወቀ ይሆናል።
የበፍታ ቀሚስ እየሠራች ትሸጣለች፥ ለነጋዴም ድግ ትሸጣለች።
ብርታትና ከበሬታ ልብስዋ ነው፤ በኋላም ዘመን ላይ ትስቃለች።
አፍዋን በጥበብ ትከፍታለች፤ የርኅራኄም ሕግ በምላስዋ አለ።
የቤትዋንም ሰዎች አካሄድ በደኅና ትመለከታለች፥ የሀኬትንም እንጀራ አትበላም።
ልጆችዋ ይነሣሉ፥ ምስጋናዋንም ይናገራሉ፤ ባልዋ ደግሞ እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል፦
መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ፥ አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ።
ውበት ሐሰት ነው፥ ደም ግባትም ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች።
ከእጅዋ ፍሬ ስጡአት፥ ሥራዎችዋም በሸንጎ ያመስግኑአት።”

## ስለዚህ አንቺ ሴት ሆይ እንደዚች ሴት ልባም ሁኚ!

**ይህን በህይወታችን ይሁን፦**

- **እጮኝነታችን እግዚአብሔርን ካላከበረ እጮኝነት ይቅርብን።**
- **ትዳራችን እግዚአብሔርን ካላከበረ ትዳር ይቅርብን።**
- **ልጆቻችን እግዚአብሔርን ካላከበሩ ልጅ ይቅርብን።**

**ኤልዛቤል ትዋረድ!!!!**

# ትዳራችሁ በቅድስና እና እግዚአብሔርን በመፍራት የተባረከ ይሁን!!

## ሰው መሆን ለሀገር

**ሰው የሆነ ሰው፡-**

- **እግዚአብሔር ለሀገሩ ለገባው ቃል ማስፈጸሚያነት ያገለግላል።**
- **እርሱ በሚገዛበት ወቅት በምድሪቱ ጉቦ፣ ስርቆት እና ፍትህ ማጣት አይኖርም።**
- **የእግዚአብሔርም አይኖች በምድሪቱ ላይ ይሆናሉ።**
    - **መዝ 68፥31**
        - “መኳንንት ከግብጽ ይመጣሉ፤ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።”

# ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች!!

# የቅድስና ትውልድ

## ሳምንት ሶስት

## ርዕስ፡ ቅድስና ለእግዚአብሔር

- **የቅድስና እድሜ ከእግዚአብሔር እድሜ እኩል ነው። ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ቅድስና ማንነቱ ነው።**
- **እግዚአብሔር ለመቀደስ ሞክሮ የሚቀደስ አምላክ ሳይሆን ከአለማት መኖር በፊት እንዲያው በራሱ ቅዱስ ነው፤ እርሱ ባለበት ቅድስና አለ።**
    - **ዘሌ 19፥2**

“ለእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ እንዲህ በላቸው፦ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ።”

- **በአብ ፈቃድ በወልድ እስከ ሞት መተዘዝ በመንፈስ ቅዱስ ስርፀት የሆነ ድነት አለን።**

- **እግዚአብሔር ያዳነን ለርሱ ቅዱሳን እንሆንለት ዘንድ እንጂ የሰው ልጅ ያለ ቅድስና በጥፋቱ እንዲቀጥል ፈቃድን ለመስጠት አይደለም።**

- **እግዚአብሔር ፅድቅን ከፀጋ ጋር ሰጥቶን ቅድስናን ከኛ ይጠብቃል።**
    - **1ጴ 1፥15-16**
        - “ዳሩ ግን፦ እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ።”

# አለመቀደስ የእግዚአብሔርን ማንነት መሳደብ ነው!

## ከምን እንቀደሳለን?

- ከሀጥያት
    - ዕብ 12፥1-2

“እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፥ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፥ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልከተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።”

- ከአለም
    - ሮሜ 12፥2
        - “የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።”
    - ነጢሞ 4፥7
        - “ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ። እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ።”

# የቅድስና ትውልድ

- **ከራስ ፍላጎት**
  - **ምሳ 16፥32**
    - “ትዕግሥተኛ ሰው ከኃያል ሰው ይሻላል፥ በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማ ከሚወስድ ይበልጣል።”

## ለምን እንቀደሳለን?

- **በሲኦልና በሰይጣን ፍራቻ ለመቀደስ መሞከር ሞኝነት ነው። ይልቁንም ለክርስቶስ ፍቅር ምላሽ ለመስጠት በሙሉ ልብ መቀደስ ተገቢ ነው።**
- **በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ለማግኘት መቀደስ አለብን።**
  - **ዘፀ 28፥36-38**

“ከጥሩ ወርቅም ቅጠል የሚመስል ምልክት ሥራ፥ በእርሱም እንደ ማኅተም ቅርጽ አድርገህ፦ ቅድስና ለእግዚአብሔር የሚል ትቀርጽበታለህ። በሰማያዊም ፈትል በመጠምጠሚያው ፊት ላይ ታንጠለጥለዋለህ። በአሮንም ግምባር ላይ ይሆናል፥ አሮንም የእስራኤል ልጆች በሚያቀርቡትና በሚቀድሱት በቅዱስ ስጦታቸው ሁሉ ላይ ያለውን ኃጢአት ይሸከም፤ በእግዚአብሔርም ፊት ሞገስ እንዲሆንላቸው ቅጠል የሚመስለው ምልክቱ ሁልጊዜ በግምባሩ ላይ ይሁን።”

- **ለመንፈስ ቅዱስ ንፁህ መቅደስን ለመስጠት**
  - **1ቆሮ 3፥16**
    - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?”

# የምንቀደሰው ለሰው አፍ ፍራቻ ስንል ሳይሆን ለእግዚአብሄር ለአምላካችን ለርሱ ፍቅር ምላሽ ስንል ነው!

# የቅድስና ትውልድ

## በእምነት ይታየኛል

- ሀገሬ ኢትዮጵያ በእኔ ዘመን እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ስትዘረጋ
- ይታየኛል የዘረኝነት ጠላት የሆነ ትውልድ ሲነሳ
- ይታየኛል ትውልድ ለአምላክ በሙሉ ልቡ ሲቀደስ
- ይታየኛል ወንጌል እንደ መጀመርያው የቤተ-ክርስትያን ዘመን እንደ ሰደድ እሳት ሲቀጣጠል
- ይታየኛል በትምህርት ንፋስ ማይነቃነቅ ትውልድ ሲነሳ
- ይታየኛል የሀገሬ ኢትዮጵያን እዳ የሚከፍል እውነተኛ ክርስትያን ባለ-ሀብት ሲነሳ
- ይታየኛል እውነተኛ ተሀድሶ ለቤ/ክ ሲሆን
- ይታየኛል በአምላኩ ማይደራረር ትውልድ ሲነሳ
- ይታየኛል የአምላክ መንፈስ በምድሬ ላይ በሙላት ሲሰራ

# ይህ ትውልድ አንተ ነህ!

# ይህች ትውልድ አንቺ ነሽ!

# ልባርካችሁ

- እግዚአብሔር ዘመናችሁን ይባርክ!
- እግዚአብሔር አገልግሎታችሁን ይባርክ!
- እግዚአብሔር በቅድስና ህይወት ይባርካችሁ!
- እግዚአብሔር በፍሬ ይባርካችሁ!
- እግዚአብሔር ፊቱን ያብራላችሁ!
- እግዚአብሔር ይራራላችሁ!
- እግዚአብሔር የእጮኝነት ጊዜአችሁን ይባርክ!
- እግዚአብሔር የትዳር ዘመናችሁን ይባርክ!
- እግዚአብሔር የምትወልዷቸውን ልጆች ይባርክ!
- የእግዚአብሔር ምህረት ለዘላለም በቤታችሁ ይሁን!
- በዘመናችሁ ኢየሱስ ብቻውን ይክበር!
- በምድር የመጨረሻ ቃላችሁ ኢየሱስ ያድናል ይሁን!

# በጣም እወዳችኋለሁ!

# ቅድስና ለእግዚአብሔር